# ሰሚ ቢገኝማ........
# “ምከረው ምከረው ካለዚያ መከራ ይምከረው!
# በአቶሰውየው  ሰሜን አሜሪካ

---

ያገሬ ሰው ሲተርት “ምከረው ምከረው ካለዚያ መከራ ይምከረው! ” ይላል። ይሄ ደግሞ የቅርብ ዘመድ ወይም ወዳጅ እንዳይጎዳበት በቅንነት ተነሳስቶ በግልጽ በኑሮውም ሆነ በማናቸውም ጉዳይ ተመላልሶ ምክር ወይም ተግሣጽ አድርጎ ተመካሪው አልሰማ ብሎ ሲያስቸግረው የመጨረሻው ደረጃ ላይ ሲደርስ የሚተርተው ነው። ለዛሬው ርዕስ መነሻ የሆነኝ በቅርቡ “ኢሕአፓን አንድ ለማድረግ የተደረገው ልዩ ጉባኤ በድል ተጠናቀቀ” (ሙሉውን መጣጥፍ ዝቅ ብለው ያንብቡ) በሚል ርዕስ የኢሕአፓን አርማ እያውብለበለበ ዛሬ ደግሞ መጠሪያውን ቀይሮ ማለትም “ከኢሕአፓ ዴሞክራሲያዊ“ ወደ “ኢሕአፓ አንድነት” ብቅ ያለው የፍርሻ ስብስብ በቅርቡ ባወጣው መግለጫ ላይ ያለኝን አስተያየት ለመስጠት ነው። ይህንን የፍርሻ ስብስብ የጸነሱት ወገኖች ገና ሲጀምሩት ከዛሬ 8 ዓመት ጀምሮ አቅጣጫቸውን እንዲያስተካክሉ በተለያዩ መጣጥፎቼ በማሳሰብ አንዳንዴም ጠንከር ያለ ተግሣጽ ያዘሉ አስተያየቶች በማቅረብ፤ ያም ሲሆን ዕውነታው ስሜታዊ ሳይሆን በቅንነት ላይ በተመሠረተ ማስረጃ ካለምንም ለቀቅተኝነት ለማመላከት ሞክሬአለሁ። በተለያዩ ጊዜአት ላቀረብኳቸው ትችቶችና ሂሶች ራሳቸውን ከማሻሻል ይልቅ በይበልጥ እኮራበት የነበረውን ያራሳቸውንና የትግል ታሪካቸውን ለመቅበር መሯሯጣቸው አሳዝኖኛል። እነሆ በዕልህ መቃብራቸውን ቆፍረው ጨርሰዋል። አንድ እንዲያዝልኝ የምፈልገው እነዚህን ወገኖች ስተች ተቃወምነው የሚሉት ክፍል <u>**ፍጹም ነው ለማለት አይደለም**</u>። ማንም ፍጹም አይደለምና። ይልቁንም በማንኛውም ምክንያት ራሳቸውን በድርጅቱ ውስጥ ማስቀጠል ያልቻሉ ወገኖች በግለሰብም ሆነ በቡድን በሕብረተሰባችን ውስጥ ሕጋዊነት ካላቸው (**legitmacy**) እኩል ቦታ ሊኖራቸው በፍጹም አይችሉም።  ብዘውን ጊዜ ለትችቴ የሚሰጠኝ መልስ አንተ የተቃወምነው ወገን አጋር ስለሆንክ አድሎአዊ አመለካከት አለህ በማለት የማቀርበውን ፍሬ ነገር ለማሳነስ የሚደረገው ጥረት አሁንም በተሳሳተ አቅጣጫ የሕዝቡን ትግል የሚከፋፍሉ ወገኖች ተጠያቂ ላለመሆን የችግሩ መነሻና መድረሻ የሚያደርጉት መስታወት ሆኖ የነሱንም ስህተት የሚጠቁመው ላይ ለመሆኑ በማያጠራጥር አስተምረውኛል። ስለሆነም ከስህተት ለመማር ትችትንና ሂስን ከማድመጥ ይልቅ ዝም የማሰኘት ዘመቻ መክፈቱ ቀሏቸዋል።

አልበርት አንስታይ ዕብደት ምን እንደሆነ ሲገልጽ “አንድን ነገር በአንድ መንገድ ብቻ ደጋግሞ ደጋግሞ በመሥራት የተለየ ውጤት ይመጣል ብሎ መጠበቅ ነው” ይል ነበር። ወይንም በእንግሊዝኛው “The definition of insanity is doing the same thing over and over again, but expecting different results - Albert Einstein -” በተቃዋሚው ወገን የሚሠራውን በቅንነት ላስተዋለ የዕብዶች ጫጫታ ብዛት ሀገሩን ወዳድ ወገኔን ግራ አጋብቶ ሁሉንም ከትግሉ አርቆ እንዲሸሽ ቢያደርግ አይገርመኝም። የሀገራችንን የፖለቲካ መሪነት ለእብዶች አስረክበን ኢትዮጵያዊው ኃይል ተዳክሞና ተበታትኖ የወያኔዎች መጫወቻ ሆነናል ብዬ ባስቀምጥ ማጋነን አይሆንም። ለዚያ ሁናቴ ደግሞ ብዙ ምሳሌዎችን መደርደር ይቻላል።

እስኪ "ኢሕአፓ ዴሞክራሲያዊ" ወይንም ደግሞ በአዲሱ መጠሪያቸው "ኢሕአፓ አንድነት" በሚል ጥላ ስር ተሰባሰብን የሚሉን ወገኖች ስህተታቸው ምን እንደሆነ ለመጨረሻ ጊዜ ላስቀምጥ።

- ቀድመው ከነበሩበት ድርጅት ኢሕአፓ ወጥተው ለብቻቸው ተገንጥለው መውጣታቸውና ድርጅት መሥርተው መንቀሳቀሳቸው ሙሉ ዴሞክራሲያዊ መብታቸው ስለሆነ ማንም ሊቃወማቸው አይገባም። ሲሆን ሲሆን በአንድ ድርጅት ውስጥ የሚሰባሰብ ወገን ሁሉ በአንድ ሰው ሳንባ የማይተነፍስ ወይንም አዕምሮ የሚያስብ ስላልሆነ የማይስማሙባቸው ነጥቦች ሲኖሩ ተከራክረው አብዛኛው የሚደግፈው ሀሳብ በድርጅቱ በሥራ ይውላል። ያ ማለት ደግሞ የተነሱ ልዩነቶችን ወይም አማራጭ ሀሳቦች ዕውነታ ስለማይቀይር ሀሳቡ ውድቅ የሆነበት ወገን ያ ሀሳብ በአብዛኛው ተቀባይነት እንዲኖረው በድርጅቱ ውስጥ እንቅስቃሴ ማድረግ ሙሉ መብቱ ይነፈጋል ማለት እንዳልሆነ ሁሉ፤ በአብዛኛው ተቀባይነት ያገኘውን ደግሞ በሥራ ላይ ማዋል ግዴታው እንደሆነ ማወቅም ተገቢ ነው። አንዳንዴ ደግሞ የተነሳው ጥያቄ የውስጥ አንድነት የሚያናጋ ከሆነ በቀላሉ ከ51 በመቶ በላይ ድምጽ እስተተገኘ ብቻ በሚልም መግፋቱ ከጠቀሜታው ጉዳቱ ስለሚመዝን ጊዜ የሚፈታውም ስለሚኖር የአባላት የንቃት ሁናቴና ግንዛቤ የሚመቻችበት ወቅት መጠበቁም ትልቅ ችሎታ ነው።

  በተለያዩ መጣጥፍና መድረኮች እንደምሰማው ከሆነ በኢሕአፓ ውስጥ ከተነሱት አከራካሪ ሁናቴዎች መካከል አንዱ የልዮነት መነሾ በአንድ ወቅት በድርጅቱ ውስጥ አፊዳፊት ፈርመን በወያኔ ስርዓት ውስጥ ሕጋዊ ሆነን ለምን አንሠራም የሚሉና ከወያኔ ጋር በምንም መልኩ መሥራት አይቻልም በሚሉ መካከል በተነሳው ክርክር አብዛኛው የድርጅቱ አባላት ኢሕአፓ ከወያኔ ጋር መሥራት አይችልም በሚለው ሀሳብ መስማማቱና አቸናፊ ሆኖ በመውጣቱ ያንን ተቀብለው በሥራ ላይ ከማዋል ይልቅ በድርጅቱ ወስጥ ተገንጣይ ቡድን (አንጃ) ፈጠሩብን የሚሉ ክሶችና ንትርኮች ናቸው የሚሉም አሉ። በዚህ ነጥብ ላይ በኔ በኩል በድርጅቱ ውስጥ ስለሌለሁበት ይሄ ትክክል ወይንም ያኛው ማለት አልችልም። በዚህም የተነሳ አባላት ድርጅቱን ጥለው ቢወጡ ምንም ችግር የለኝም። ይልቁንም ይህንን በሚመለከት የሚነሱ ዕውነት ወይም ውሸት ነው የሚባሉትን አንዴ ጥግ ለማስያዝ የድርጅቱ አመራር በጊዜው ይህንን አስመልክቶ የቀረቡ ጽሑፎችንና ነጥቦችን ለሕዝቡ ይፋ ቢያደርግ ለሁሉም ትምህርት ሰጪ ይሆናል ብዬ አምናለሁ። የተለያዩ አሉባልታዎችና የውሸት ወሬዎችም ድርጅቱን ስለሚጎዱ በየጊዜው ድርጅቱ ለሕብረተሰቡ እውነታዎችን በተደጋጋሚ ማቅረቡ ጥሩ ነው ባይ ነኝ። የልዮነቶች ምክንያቶች እንደ ምሳሌ ይሄ ይሁን እንጂ በርካታ ክሶችን በአደባባይ በተለየ ከድርጅቱ ወጥተናል በሚሉን ወገኖች አማካኝነት ብዙ ሰምቻለሁ።

- እንግዲህ ይህንን ድርጅቱን ጥለው የመውጣት ዴሞክራሲያዊ መብታቸውን የምታከብር ከሆነ ታዲያ እነዚህን ወገኖች ለምን ትተቻለህ? እንዲያውም አፍራሽ የሚል ቅጽል ትሰጣቸዋለህ ብለው ለሚጠይቁ ደግሞ እነሆ፡-

  በቅርቡ በአንድ የሰሜን አሜሪካ ከተማ ከሁለት ተከፍሎ አዲስ ቤተ-ክርስቲያን ከመሠረቱት ጋር አብራ ከመሠረተች ወገን ጋር ስንጨዋወት፣ በቤተክርስቲያን ውስጥ ለመከፈል ምክንያት የሆነውን የቀኖና ጉዳይና ከዚህም ጋር አያይዞ ያስከተለው ፍጥጫ ለብዙ ዓመት በቤተ ክርስቲያኑ ተሰባስበው ተሳስረው የነበሩ ምዕመናን ሆድና ጀርባ መሆን አሳዛኝነቱ ብቻ ሳይሆን ሁለቱም ወገኖች ያጡት ትልቅ ነገር መኖሩን በጭውውታችን ተማምነናል። ከሁሉም በላይ ቤተ-ክርስቲያኑ ከተቆረቆረበት ጊዜ ጀምሮ በያንዳንዱ ቤተሰብ ተወልዶ ለክርስትና ከዚያም በዕድገት በመዘምራንነት በሌሎችም ሕብረ-ሰቡ ተሳስሮበት የነበረው የኢትዮጵያዊ ባሕል እዚህ አገር ለተወለዱ ልጆች የኢትዮጵያዊ ቅርስ የሚተላለፍበት የሕብረተሰቡ መሠረት ቤተ-ክርስቲያን ሲከፈልና ወገኖች እንደጠላት የሚገለማመጡበት ሁናቴ ለአዲሱ ትውልድ የሚሰጠው ምሳሌነት በግምት ሲገባ ማንኛውም ወገን አቸናፊ ሊባል እንደማይቻል መገመት ችለናል። በእርግጥ ያ እንዳለ ሆኖ ተክፍሎ የሄደው ወገን

የቀድሞው ቤተ-ክርስቲያን ንብረትም ሆነ ተቀማጭ ገንዘብ ይሰጠኝ ለማለት (በሕግም እንኳን ለመጠየቅ) አስቸጋሪ መሆኑ አይቀሬ ነው። እኛ ኢትዮጵያውያን የምንሄድበት ሁላችንም ልብ ልንለው የሚገባ ነገር አለ። ሀገራችን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የለምና ያንን ለማምጣት እንታገል ሲባል፣ በዘር ተከፋፍለን፣ በክልል ተሸንሽነን በክልላችን ነፃ መውጣት የዴሞክራሲያዊ መብት መሠረት ነው በሚል ፈሊጥ፤ ዛሬ በይፋ የከሰረው የጎጥ ፖለቲካ የገደል አቅጣጫ እንመርጣለን። አንዳንዶቻችን ኢትዮጵያን እንደ አዲስ በሬፈራንደም እንመሠርታለን የሚሊ እብዶችን ካልደገፍን ሞተን እንገናለን እንላለን። ከቤተ-ክርስቲያን ጀምረን ወያኔን ለመጣል በመካከላችን መተማመንን በመፍጠር ጠንካራ ኢትዮጵያዊነትን ማዕከል ያደረገ ድርጅት ያስፈልገናል ብለን ስንሰባሰብ በድርጅቱ ውስጥ የተለያየን ሰዎች ነንና አለመስማማት ሲነሳ ያንን አለመስማማት አርቀን፣ በድርጅት ለመሳባሰብ ያነሳሳን ዓላማ ከሁሉም በላይ ስለሆነ በዋናው ዓላማችን ጸንተን ድርጅታችንን የበለጠ አጠናክረን የምንወጣበትን ዘዴና መላ ከመፈለግ ይልቅ በልዩነታችን ላይ ብቻ ትኩረት አድርገን የነበርንበትን ድርጅት አፍርሰን አዲስ መፍጠር መፍትሄ ብለን ጠቃሚ ድርጅታችንን በየተራ በመቦርቦር የረባ ነገር ሳንሠራ ዕድሜአችንን እናጠፋለን። ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ እንዲሉ ከመሥራት ይልቅ የሚሠሩት ላይ እጣታችንን እየጠቆምን ስንሳለቅ ጊዜ ያልፋል። እነሆ ወያኔም 24 ዓመት ቀጥቅጦ ገዝቶናል። ይኸንን እንደ ህብረተሰብ ልንመረምረው የሚገባ የሁላችን ህመም ነው ባይ ነኝ።

ከስምንት ዓመት በፊት "ኢሕአፓ ዴሞክራሲያ" ዛሬ ደግሞ "ኢሕአፓ አንድነት" ብሎ ብቅ ማለት ተግባረ ጥፉን በስም ይደግፉ ካልሆነ በስተቀር ሰሞኑን የተሠራው ሥራ ኢሕአፓን አንድ ማድረግ እንዳልሆነ ያልተረዱት በባልቲሞር የተሰበሰቡትና ደጋፊዎቻቸው ብቻ እንጂ ወዳጅም ጠላትም ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ ነው ነገሩ። ለመሆኑ ባለፈው 8 አመት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል የሚጠቅም ምን ሠራችሁ ቢባሉ ምን ይሉን ይሆን? እንዲያውም የወጡቱ በአንድነት መቀጠል አቅቷቸው በጎጥ ሳይቀር ብትንትናቸው እንደወጣ የአደባባይ ሚስጥር ነው። ዛሬስ ኢሕአፓን አንድ ለማድረግ የሚለው ሽር ጉድ ዋናውን ድርጅታቸውን ሳይጨምር እንዴት ሊሆን ይችላል ብለው ያስባሉ? ማንንስ ለማታለል? ከራሳቸው በስተቀር። ወይንስ የሚያቅ የለም፣ ቢኖርም ማን ሊናገር ደግሞ የሚል ትዕቢት የሞላበት የሕዝብ ንቀት? የሚሰማ ከተገኘ......እነዚህ ወገኖች ለኢትዮጵያ ሕዝብ የዴሞክራሲያዊ ትግል ከልባቸው አስበው ከሆነ (ለኔ እንኳ ያ አጠያያቂ ከሆነ ሰንበትበት ብሎብኛል፣ እንዲያውም በአንድ ጽሑፌ እንዳስቀመጥኩት ወያኔ ወያኔ ሸተውኛል ባይ ነኝ) የስብስባቸውን ስም ኢሕአፓ ማለት እንደማይችሉ ተረድተው የተለየ ስም ሰጥተው ከኢሕአፓዎች ጋር ወደፊት በዓላማ ከተገናኙ በግንባር ለመሥራት ሊታመኑ የሚችሉበትን ሁናቴ ባመቻቹ ነበር። ያ ደግሞ ለትግሉ ጉልበት ስለሚሆን እንደኔ ዓይነቱ የማይደግፍበት ምክንያት አይታየኝም። እንዲያውም አብረው እንዲሠሩ ግፊት በተደረገ ነበር። ኢሕአፓን ትተው ከወጡ በኋላ እኮ ሌላ ድርጅት መሥርተው በግንባር ከኢሕአፓ ጋር የሠሩ ወገኖች እንደነበሩ ሁላችንም የምናውቀው ታሪክ ነው። ኢሕአፓ ከምሥረታው ጀምሮ የተለያዩ ቡድኖች ግንባርና ውህደት መሆኑን ዛሬ ለነአቶ መርሻ ላስተምር ብል ልጅ ለናቷ ምጥ አስተማረች ይሆናል። ታዲያ ምን ነካቸው? የክፍሉ ታደሰ ወዴት እየሄድን ነው? ጥያቄ ተቀይሮ ወዴት እየሄዳችሁ ነው? ብሎ በሲምፖዚየማቸው ቢያቀርብ ኖሮ ባለፈው ጊዜ ያቀረብኩት ጽሑፍ ውስጥ የዘረዘርኩለትን ትችት ተመልሼ እንድመረምር ያደርገኝ ነበር። ላለፉት 8 ዓመታት የተንከለከሉበት ጎዳና ጠላትን ያስደሰተ ወዳጅን ያሳዘነ ለመሆኑ ሳይረዱ የቀሩ ስለማይመስለኝ እንደእኔ ዓይነቱ ወያኔ ወያኔ ሸተታችሁኝ ቢል አይፈረድበትም።

አንዳንድ ወገኖች እንዴ ለምንድር ነው ኢሕአፓ ነን ማለት የማይችሉት ብለው ሊሟገቱ ይሞክሩ ይሆናል። ይሄን አባዜ እኮ ነው ትክክል አይደለም፣ አፍራሽነትም ነው የምለው። ሀገር ወዳዶች የምንፈለገውን ተጠናክሮ መውጣት ያለበትን ኢትዮጵያዊ ኃይል የሚያዳክም ስለሆነ ነው።

ላብራራ፡- በኢሕአፓ ውስጥ መቀጠል አልችልም ብሎ ድርጅቱን ለቆ የወጣ ግለሰብም ይሁን ቡድን፣ ወይንም ደግሞ ድርጅቱ ውስጥ ያለውን ሕግና ደንብ አላከብርም ብሎ ከድርጅቱ ራሱን አስፈንጥሮ ያስወጣ ግለሰብም ሆነ ቡድን የድርጅቱን ስም፣ ንብረት ሆነ ማንኛውንም ነገር የኔ ነው ማለትማ አግባብነት ሊኖረው አይችልም። ከላይ ከሁለት የተከፈለው ቤተ-ክርስቲያን ንብረት ወይንም መዋጮ ማስመለስ ዓይነት ጥያቄ ምን ሊሆን እንደሚችል ያጤኗል። ተገንጥለው የወጡት በድርጅቱ ውስጥ የብዙኃኑን ድምፅ ይዘው ቢሆኑ ኖሮ እኮ ለቀውም አይወጡም ነበር። ስለሆነም የድርጅቱን ስም ይዘው መቀጠል አይችሉም። የሕግ የበላይነት ብሎ ማነብነብ ብቻ ሳይሆን እኮ በሕብረተሰባችን የማናልፋቸው መሥመሮች መኖራቸውን ማወቅ፣ የሚቀጥለውም ትውልድ ከኛ ሊማራቸው የሚገቡ ምግባራትን ኃላፊነት በተሞላው በተግባር ማሳየት የሚጠበቅብን ነው። ይሄ እኔ ከሞትኩ ስርዶ አይበቀል እንደምትለው አህያ ድርጅቱን እኔ ከሌለሁበት ይፍረስ ትልቅ ነውር ነው። እንዲያውም በኢሕአፓ ውስጥ አለፍን የምንል በትምህርት ለአዲሱ ትውልድ ልናስተምረው የሚገባ ***ህመማችን*** ነው። መሪዎቻችን ተወደደም ተጠላ ለሕዝቡ ተጠያቂነት አለባቸው። ይህንን ዓይነቱን የማናለብኝነት የዕልህ ሥራ መፍቀድ የተበታተነውን ትግል ሂደት ማራዘም፣ ትግሉንም ለኢትዮጵያነት ጠላት ምት ማመቻቸት ነው። ስለሆነም በአንድ ድርጅት ውስጥ የተሰባሰቡ ወገኖች የድርጅቱን ሕግና ደንብ ከሁሉም በላይ የብዙሃኑን ድምጽ ማክበር ይጠበቅባቸዋል። ያንን ማክበር ካቃታቸው ምንም ዓይነት ፕሮግራም ቢደረድሩ ማንነታቸውን የሚገልጽ በተሳተፉበት ድርጅት እንኳ ዴሞክራሲያዊነትንና የህግ የበላይነትን ማንጸባረቅ ካቃተቸው የሀገር መሪ በሚሆኑበት ወቅት በወገን ላይ ምን ያህል ጉዳት ሊያደርሱ መቻላቸውን የሚያስቀምጥ አመላካች ባህርይ ስለሆነ ልንጠነቀቅ ይገባል። ሕብረተሰቡም ሊተቻቸው፣ ሊጠርባቸው ይገባል። ለኢትዮጵያ ሕዝብ እየታገልን ነው እስካሉን ድረስ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሊጠይቃቸው ይችላል። አንተ የድርጅት አባል እስካልሆንክ ድረስ ምን አገባህ ማለትም አይቻልም።

**ለማጠቃለል፡-**

ስሚ ቢገኝማ ገና ከጅምሩ ኽረ እየተስተዋለ ቀዩ መስመር እየተጣሰ ነው ተብሎ ነበር።እነሆ ኢሕአፓ ዴሞክራሲያ የሚለው ውሸት አልሠራ ብሎ ዛሬ ደግሞ ኢሕአፓ አንድነት የሚል ሌላ ወንዝ የማያሻግር ውሸት ተይዞልናል። **<u>በኔ እምነት ይሄ አፍራሽነት ነው።</u>** ኢሕአፓን አንድ ለማድረግ ሳይሆን በሕብረተ-ሰቡ ውስጥ ውዥንብርን የሚነዛ፣ የኢሕአፓን ተሰሚነት የሚወስንና ጠላቶቹ እንደሚፈልጉት ኢሕአፓን የሚያዳክም፣ እያዳከመም ያለ አደገኛና መሠሪ እንቅስቃሴ ነው። ኢሕአፓን አንድ በማድረግ ስም እውነተኛዎቹንና ከትግሉ ያልተለዩትን ኢሕአፓዎች ወደ ጎን ገፍትሮ የኔ ቢጤ ፈርጣጩን፣ ከሃዲውንና ጨለምተኛውን፣ እንዲያም ሲል ከወያኔና ከዘረኞች ጋር የሚተሻሸውንና ተላልሱም ሳይሳካለት ተተፍቶ የሚንገዋለለውን ልምጥምጥ ሁላ ሰባስቦ ኢሕአፓ ነን ብሎ ብቅ ማለት የትም አያደርስም! ስለሆነም ሲለወገዝ ይገባዋል። ዛሬ ዛሬ እንኳን እንደመጀመሪያው ጊዜ ያዳቆናቸውም ሁሉ የሸሻቸው ይመስላል። ድሮውንም ዶሮን ሲያታልሏል በመጫኛ ጣሏት እንዲሉ ለአንጃኞች ድረ-ገጾቻቸውን፣ ራዲዮና የመሳሰሉ መድረኮቻቸውን ቢለግሷቸው ኢሕአፓን ያዳከሙና መሳለቂያ ለማድረግ እንደሁ እንጂ አንጃኞችን አምነው ለማቀፍና ለመደገፍ አልነበረም። የወያኔ ጋዜጦች ሳይቀሩ እኮ አንጃኞች የሚበትኑትን ሲያትሙላቸውና ሲያሰራጩ ታዝበናል። የኢሕአፓን ኢትዮጵያዊ አጀንዳ የሚጠሉ ሁሉ አንጃኞችን አያምኑም። ሊጠቀሙባቸው እንጂ። ያ መሆኑን ያልተረዱ ማፈሪያዎቹ አንጃኞቹና መሰሎቻቸው ብቻ ናቸው። ለሌሎቻችን ደግሞ ይኼ መሠሪ ጨዋታ ግልጽ ከሆነ ውሎ አድሮአል።

**ኢሕአፓ አንድና አንድ ብቻ ነው!** ኢሕአፓን በማንኛውም ዓይነት ምክንያት ለቆ መውጣት የየግለሠቡ ሙሉ መብት ነው።በስሙ መነገድ ግን በየትኛውም ዓይነት መንገድ ያስጠይቃል። የኢትዮጵያን ትግል ለማሽመድመድ እንደሚሰበቅ ጦር ሀገር ዋዳድ ሁሉ ሊያወግዘው ይገባል። ከዚህ ዓይነት ቡድን ጋር የሚወግን ግለሰብ ወይም ቡድን በእኔ ዕምነት ካለምህረት ከዚሁ የምመድበው ነው። በዓለም ዙሪያ የተሠረቀን ዕቃ ከሌባ ላይ የገዛ ከሌባ እኩል ለፍርድ ይቀርባል። ካለምክንያት አይደለም። ሸንጎ የሚባለውም ቡድን ይህ አንጃ የማይገባውን የኢሕአፓን ስምና አርማ ይዞ የስብስቡ አባል ማድረጉን እስከቀጠለ ድረስ በአፍራሽነት የምመድበው ቡድን ነው። ይህንን ለማስተካከል ደግሞ ቁልፉ በአንጃኞችና በደጋፊዎቻቸው በሸንጎውም እጅ ነው። ኢሕአፓ የሚለውን ስም አስቀምጠው በአዲስ ስም ሲንቀሳቀሱ ብቻ ነው ተቀባይነታቸው ሊረጋገጥ የሚገባው። ያንን አድርገው ሲመጡ ሁላችንም በገምቢነት ኃይል በትግሉ አጋርነት ረድፍ እናሰልፋቸዋለን።  የሚሳተፉበትንም እንደ ሸንጎ ዓይነቱን ስብስብ የክብር ቦታ ያሰጣሉ። ካለበለዚያ እነሱም ደጋፊዎቻቸውም አፍራሾች ይሆናሉና ልንታገላቸው ይገባል ባይ ነኝ።

አሁንም ኢሕአፓ አንድና አንድ ብቻ ነው።

ሞት ለበታኞች! ለአንጃኞችና ለዘረኞች!

አቶሰውየው ከሰሜን አሜሪካ (ሐምሌ 3 ቀን 2007 ዓ.ም.)

# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
# *Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*

(አንድነት/United)

ሰኔ ፳፭ ቀን ፪ ሺህ ፯ ዓ. ም
July 2, 2015

## ኢሕአፓን አንድ ለማድረግ የተደረገው ልዩ ጉባኤ በድል ተጠናቀቀ

ተከፋፍሎ የነበረው ኢሕአፓ በሜሪላንድ ክፍለ ግዛት በባልቲሞር ከተማ ለሦስት ቀናት ያካሄደው የአንድነት ልዩ ጉባኤ በተሳካ ሁኔታ ተጠናቀቀ።

ከአንድ ቀን በፊት ከተደረገው ሕዝባዊ ሲምፖዚዬም ተከትሎ ከሰኔ ፳፪ እስከ ሰኔ ፳፭ ቀን ፪ ሺ ፯ ዓ ም (June 28 - July 1, 2015) በተካሄደው ልዩ ጉባዔ ከመላው ዓለም የመጡ አባላት የተሳተፉበት ነበር።

ይህ ጉባዔ የድርጅቱን ዋና ዋና ጉዳዮች እንዲሁም በድርጅቱ ውስጥ ተፈጥሮ የነበረውን ችግርና ለመለያየት የነበሩትን ምክንያቶች በሰፊው ከመረመረ በኋላ፣ ችግሮችን አስወግዶ በአንድነት ለመታገል ወስኗል። ይህንን ልዩ ታሪካዊ የአንድነት ጉባዔ ግምት ውስጥ በማስገባት የድርጅቱ መጠሪያ ስም ኢሕአፓ (አንድነት) እንዲሆን ወስኗል።

ጉባዔው የኢትዮጵያን አጠቃላይ ፖለቲካዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሁኔታዎችን በጥልቀት ከገመገመ በኋላ፤

- ሀገሪቱ በአንድ ብሄርተኛ አምባገነን ቡድን ሥር በመውደቋ ምክንያት ሕዝባችን የቀን ተቀን ሕይወቱ አደጋ ላይ የወደቀ መሆኑን፣
- በሀገሪቱ ውስጥ መሠረታዊ የሰብዓዊና የዴሞክራሲያዊ መብቶች የተረገጡ መሆናቸውን፤ እነዚህ መሠረታዊ፤ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በጠፉበት

**P.O.Box 8141**
**Silver Spring, MD 20910**

**P.O.Box 88675**
**Los Angeles, CA 90009**

**Phone: 202- 241 2078**

**Email Address**: **eprp-democratic@eprp-ihapa.com**

ሁኔታ ነፃ፤ ፍትሃዊና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ሊካሄድ የሚችልበት ሁኔታ አለመኖሩን፤ ይህንንም እውነታ ፪ ሺ ፯ ዓ. ም ምርጫ ተብዬ እንደገና እውነታውን ማጋለጡን፣

- ይህ አምባገንነን የወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዝ በፈጠረው ሁኔታ ምክንያት ሀገራችን በጎሣ፣ ፖለቲካና በውጭ አክራሪ ኃይሎች ተጽዕኖ ከፍተኛ አደጋ ላይ መሆኗን፣
- ዜጎች ለረዢም ዘመን ሃብትና ንብረት አፍርተው ከኖሩበት ቦታ መፈናቀላቸውን፣
- በሀገሪቱ የዕምነት ነፃነት መጥፋቱን፤
- አገዛዙ በጎረቤት አገሮች ጣልቃ በመግባቱ ምክንያት አክራሪነት በሀገራችን እንዲያንዣብብ አንዱ ምክንያት መሆኑን፣
- ወያኔ/ኢህአዴግ የሀገሪቱን ዋና ዋና የኤኮኖሚ ዘርፎች በፓርቲው መዳፍ ሥር አውሎ ዜጎች በነፃነት በኤኮኖሚው መስክ ተሳትፎ እንዳያደርጉ መደረጉን፣
- አገዛዙ ኤኮኖሚው በሁለት አሃዝ አድጓል ይበል እንጂ፣ እውነታው የሚያሳየን ግን ድህነት መንሰራፋቱን፤ አብዛኛው ሕዝባችን ጠዋት በልቶ ማታ አለመድገሙን፤ ለኑሮ እጅግ አስፈላጊ የሆኑ ዕቃዎች በብቃት አለመገኘታቸውንና ዋጋቸው እጅግ መናሩን፣
- በሀገሪቱ ውስጥ በሥራ ማጣትና በኑሮ ዋስትና እጦት ምክንያት ከሀገራቸው እየተሰደዱ በባዕድ አገር ለሞትና ለዘመናዊ ባርነት የሚዳረጉ ወጣቶች ለስደታቸው ምክንያት የሆነው አምባገነኑ የወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዝ አስተዳደራዊ ብልሹነት መሆኑን ፣
- ከስልሳዎቹ በፊት ጀምሮ አርሶ አደሩ የመሬት ባለቤት እንዲሆን ብዙ መሥዋዕትነት የከፈለ ቢሆንም አሁንም አርሶ አደሩ የአገዛዙ ገባር መሆኑንና በመሬት ጥበት ምክንያት ከቀየው እየተፈናቀለ ወደ ከተማ እየጎረፈ መሆኑን፣
- የውጭ ባለሃብቶች የአገሪቱን ሃብት ከመዝረፍ በተጨማሪ ኗሪውን ሕዝብ ከቀየው በማፈናቀል ችግር ላይ እንዲወድቅ ማድረጋቸው፣
- የውጭ ባለሃብቶች ያለምንም ቁጥጥር የአገሪቱን የተፈጥሮ ደን በማውደም ሀገራችን ወደ በረሃነት እንድትለወጥ ማድረጋቸው፣
- አገዛዙ አያት ቅድማያቶቻችን ጠብቀው ያኖሯትን አገር ቆርሶ ለባዕዳን መስጠቱን፣

- ህገ-መንግሥታዊና ዴሞክራሲያዊ መብታቸውን በመጠቀም በሕጋዊ መንገድ ለመታገል የሞከሩ ዜጎች በየቦታው እየተለቀሙና እየታደኑ ወደ እሥር ቤት መወርወራቸውን፣
- በቅርቡ የተደረገውን የምርጫ ቲያትር ተከትሎ በርካታ የተቃዋሚ አባላትን በጠራራ ፀሐይ በአገዛዙ የስለላ መረብ አማካኝነት መገደላቸው የአገዛዙን አምባገነንነትና ፀረ-ዴሞክራሲነት በግልጽ የሚያመለክት መሆኑን፣

ጉባዔው ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ከመረመረና ግንዛቤ ከወሰደ በኋላ፤

- ጉባዔው የወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዝ ሀገር አፍራሽና አጥፊ ፖሊሲዎቹን በጥብቅ አውግዟል።
- ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመመሥረት፣ የወያኔ/ኢህአዴግን አገዛዝ ማስወገድ እንደሚገባ አረጋግጦ፣ የበለጠ ተጠናክሮ መታገል እንደሚገባ በድጋሚ አረጋግጧል።
- ይህን ለማስፈጸም ከተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችና ሌሎች የዴሞክራሲ ንቅናቄዎች ጋር በመተባበር መሥራት አስፈላጊ መሆኑ አጽዕኖት ሰጥቶበታል፤ ከዚህ አኳያም ኢሕአፓ (አንድነት) በኢትዮጵያ ሕዝብ የጋር ትግል ሸንጎ ውስጥ በአባልነት ለመቀጠል ወስኗል።

በመጨረሻም የአንድነቱ ጉባዔ የፓርቲውን የምክር ቤት የአመራር አባላትና የሙብት አስጠባቂ ኮሚሽን አባላትን መርጦ ጉባዔው በተሳካ ሁኔታ ተጠናቅቋል።

የተባበረ ትግል ምንጊዜም አቸናፊ ነው!